| 10ኛ አመት ቁጥር 61<br>10th Year № 61 | ባህር ዳር ሐምሌ 1 ቀን 1997 ዓ.ም<br>Bahir Dar July 8, 2005 |
|---|---|


# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

# ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE HIG

## OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA


| | | | |
|---|---|---|---|
| **የአንዱ ዋጋ ብር 4.25 Price** | **በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ** | **ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE** | **የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box** |


| **ማውጫ** | **CONTENTS** |
|---|---|
| **ደንብ ቁጥር 36/1997 ዓ.ም** | **Regulation No. 35/2005** |
| በአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት የከተማ አስተዳደሮችና የማዘጋጃ ቤት ከተሞች የሰው ኃይል ድልድል መወሰኛና ማጥሪያ ደንብ ማሻሻያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | The Amhara National Regional State City Administrations and Municipal Cities Manpower Placement Determination and Screening, Council of Regional Government Amendment Regulation. |

## ደንብ ቁጥር 36/1997 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት የከተማ አስተዳደሮችና የማዘጋጃ ቤት ከተሞች የሰው ኃይል ድልድል መወሰኛና ማጥሪያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

## REGULATION NO. 36/2005

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF THE MANPOWER PLACEMENT DETERMINATION AND SCREENING OF THE CITY ADMINISTRATIONS AND MUNICIPAL CITIES IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

በሠራተኛ ማብቃቱ ሂደት የተከሰቱትን የአፈፃፀም ጉድለቶች ለማረምና አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ ያመች ዘንድ በሥራ ላይ ያለውን የከተማ አስተዳደሮችና የማዘጋጃ ቤት ከተሞች የሰው ኃይል ድልድል መወሰኛና ማጥሪያ ደንብ ቁጥር 19/1996 ዓ.ም. ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ም/ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል::

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የከተማ አስተዳደሮችና የማዘጋጃ ቤት ከተሞች የሰው ኃይል ድልድል መወሰኛና ማጥሪያ ደንብ ማሻሻያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 36/1997 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ማሻሻያ

የከተማ አስተዳደሮችና የማዘጋጃ ቤት ከተሞች የሰው ኃይል ድልድል መወሰኛና ማጥሪያ ደንብ ቁጥር 19/1996 ዓ.ም. እንደሚከተለው በዚህ ደንብ ተሻሽሏል::

ሀ. ከደንቡ አንቀጽ 34 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 35 የገባ ሲሆን በዚሁ ተጨማሪ አንቀጽ መግባት ምክንያት ተከታዮቹ ድንጋጌዎች አንቀጽ 36፣37፣38፣ እና 39 ሆነው ተሸጋሽገዋል::

35. ልዩ ሁኔታ

1. ከዚህ በላይ በአንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 30 ንዑስ

Whereas, it has been found necessary to amend the manpower placement determination and screening regulation No. 19/2004 currently in effect so as to make it favorable for the correction of the implementation weaknesses faced during the capacitation process with regard to the employees and thereby taking of the rectification measures.

Now, therefore, the council of the Amhara National Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of art. 58 sub-art. 7 of the revised Regional Constitution, hereby issues this regulation.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as "The City Administrations and Municipal Cities Manpower Placement Determination and Screening Regulation Council of Regional Government Amendment Regulation No. 36/2005."

**2. Amendments**

The City Administrations and Municipal Cities' Manpower Placement Determination and Screening Regulation No. 19/2004 is hereby amended by this regulation as follows:

A) The following new Art. (35) is included next to Art. (34) of the regulation and, due to the insertion of this additional article, the provisions which follow subsequently are re-arranged to stand as Arts. 36, 37, 38 and 39.

**35. Special Circumstance**

1. Notwithstanding the provisions of art. 28 sub-art. 3 and-art 30, sub-art 4

አንቀጽ 4 ስር የተደነገገው ቢኖርም የማብቃቱ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ በተወሰዱ እርምጃዎች አፈፃፀም ያልተገባ ፍረጃ አጋጥሞናል ወይም አድልዎ ደርሶብናል የሚሉ የከተማ አስተዳደር ወይም የማዘጋጃ ቤት ሠራተኞች ቢኖሩ ቅሬታቸው በዞን ወይም በብሔረሰብ አስተዳደር ደረጃ ለዚሁ ዓላማ በሚቋቋም አጣሪ ኮሚቴ እየታየ ለየዞን ወይም የብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤቱ ቀርቦ ውሣኔ ያገኛል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም ከባህርዳር ከተማ አስተዳደር የሚመነጩ ቅሬታዎች ቀርበው የሚጣሩትና የመጀመሪያ ደረጃ ውሣኔ የሚያገኙት በክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ አማካኝነት ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች መሰረት በሚሰጡ ውሣኔዎች ላይ ቅር በመሰኘት የሚቀርቡትን ይግባኞች የክልሉ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ መርምሮ የመጨረሻ እልባት ይሰጥባቸዋል፡፡ ዝርዝሩ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም በቢሮው በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

hereinabove, where there are employees of City Administrations and Municipal Cities complaining to have encountered improper leveling or been subjected to discrimination due to the enforcement of measures taken after the capacitation process has come to an end, their grievances shall be examined by the grievance reviewing committee to be established for the purpose at the Zonal or Nationality administrative level and submitted to and obtain decision by the pertinent Zonal or Nationality administrative council.

2. Notwithstanding the provision of sub art 1 of this article hereof, grievances arising from the Bahir Dar City Administration shall be submitted to and obtain first-instance decision by the Regional Works and Urban Development Bureau.

3. The Regional Trade, Industry and Urban Development Bureau shall investigate into and thereby render final solutions for those appeals which might be so submitted due to the dissatisfaction of the decisions rendered pursuant to the provisions of sub arts. 1 and 2 of this article hereof. Details shall be determined by a directive to be issued by the

www.chilot.me

ለ. ከደንቡ አንቀጽ 35 ንዑስ አንቀጽ 2 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተጨምሯል::

3. የማብቃቱ ሂደት ከሥራ ከተሰናበቱና የመጦር መብት ያልተከበረላቸው ሠራተኞች 20 ዓመት የአገልግሎት ዘመንና 45 ዓመት ዕድሜ የሞላቸው መሆኑ ከተረጋገጠ የመቋቋሚያ ክፍያ የማግኘት መብት ይጠበቅላቸዋል:: አፈፃፀሙን በክልሉ መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 74/1994 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 83 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ስር ለመንግስት ሠራተኞች ከተደነገገው ጋር በተመሣሣይ የሚከናወን ይሆናል::

ሐ. የደንቡ አንቀጽ 36 ድንጋጌ ሙሉ በሙሉ የተሰረዘ ሲሆን በዚሁ አንቀጽ ስረዛ ምክንያት ተከታዮቹ አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ 36 እና 37 ሆነው ተስተካክለዋል::

3. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከሐምሌ 1 ቀን 1997 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህርዳር
ሐምሌ 1 ቀን 1997 ዓ.ም
ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ርዕሰ መስተዳድር

Bureau with the view to implementing this regulation.

B) The following new sub article (3) is included next to sub article 2 of Art. 35 of the regulation:

3. Employees who might have been dismissed from job due to the capacitation process and not entitled to pension right shall be qualified for a rehabilitation pay provided that they have attained 20 and 45 years with regard to their service and age respectively. Its implementation shall be carried out in such similar ways as has been stipulated for public employees under Art. 83, sub arts 1 and 2 of the regional civil Servants' proclamation No.74/2002, as amended.

C) The provision of article 36 of the regulation is hereby deleted in full and due to this cancellation, the Arts. Which follow subsequently are re-arranged to stand as Arts, 36 and 37 receptively.

**3. Effective Date**

This regulation shall enter into force as of July 8, 2005.

Done at Bahir Dar
This 8th day of July, 2005
Yosef Retta
Head of Government of the
Amharा National Regional State